**ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች**

(አርብ—ሁለተኛ የማለዳ ክፍለ ጊዜ)

መልእክት ሁለት

**በዘመኑ አገልግሎት በኩል**
**የተጠናቀቀውን የዘመኑን ራእይ አጥብቆ መከታተል**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- 2 ቆሮ. 3፡3፣ 6፣ 8፤ 4፡1፤ 5፡18-20፤ 11፡2-3፤
1ጢሞ. 1፡3-4፣ 18፤ ራእ. 22፡1-2፣ 14፣ 17

**I. በእያንዳንዱ ዘመን የዚያ ዘመን የሆነ ራእይ አለ፣ እኛም በዘመኑ አገልግሎት በኩል የተጠናቀቀው የዘመኑ ራእይ ስላለን፣ በዚህ ራእይ መሠረት እግዚአብሔርን ማገልገልና [ይህንን ራእይ] አጥብቀን መከተል ያስፈልገናል—ሐዋ. 26፡19፤ ኤፌ. 1፡17፤ 3፡9፤ 1 ጢሞ. 4፡6፡-**

ሀ. ዛሬ አንድ ራእይ፣ የጊዜው የሆነ፣ ሁሉን-ወራሽ የሆነ ራእይ፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ራእይ ስላለን በአንድ ልብ መሆን እንችላለን—ኤፌ. 1፡17፤ 3፡2፣ 9፤ ራእ. 21፡10፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ ሮሜ. 15፡6፤ 1 ቆሮ. 1፡10፤ ሐዋ. 26፡13-19፤ ፊልጵ. 3፡13-14።

ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ገዢው ራእይ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ሰማያዊው ራእይ ነው፣ ይህም እንደ የእርሱ ብዜት ከእርሱ ጋር አንድ አይነት ይሆኑ ዘንድ በመለኮታዊው ሥላሴው እንደ አብ፣ በወልድ ውስጥ በመንፈስ ሕይወታቸው እና ባህሪያቸው ለመሆን ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን ለማደል ከልብ መሻቱ ጋር የሆነው የእግዚአብሔር ውጥን ነው፣ ይህም ለእግዚአብሔር ሙላት፣ ለእግዚአብሔር መገለጥ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀውን እንደ አዲሱ ሰው ሕይወታዊ አካል፣ የክርስቶስ አካል ለመሆን ነው—ኤፌ. 4፡4-6፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10።

ሐ. "እኔ [ዊ. ሊ.] ለወንድም ኒ እንዲህ አልኩት፣ 'ምን አልባት አንድ ቀን አንተ ይህን መንገድ ባትወስድ እንኳ፣ እኔ ግን ይህን መንገድ እወስዳለሁ። ይህን መንገድ የምወስደው በአንተ ምክንያት አይደለም፣ እንዲሁም ይህን መንገድ በአንተ ምክንያት አልተወውም። ይህ የጌታ መንገድ እንደሆነ አይቻለሁ። ራእዩን አይቻለሁ'" (*The Vision of the Age* ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 50 የተወሰደ)።

**II. ጌታ በአሁኑ ጊዜ ባለው ምለሳው የሰጠን ራእይ፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ሁሉን-ያካተተ ራእይ ከከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ መጠናቀቁ ጋር—ከአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ራእይ ጋር—ነው—ምሳ. 29፡18፤ ሐዋ. 26፡18-19፤ 22፡15፤ ራእ. 21፡2፣ 9-11፡-**

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጥልን ነገር ጥቅል-ድምር አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት፤ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የመላው መጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ አጠቃላይ ውቅር ናት—ዘፍ. 28፡10-22፤ ዮሐ. 1፡1፣ 14፣ 29፣ 32፣ 42፣ 51፤ ራእ. 21፡3፣ 22።

ለ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን መኖራችን አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን እንሆን ዘንድ ነው፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን መሥራታችን ደግሞ በሚፈስሰው ሦስታንዱ አምላክ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን እንገነባ ዘንድ ነው—ኤር. 2፡13፤ ዮሐ. 4፡14፤ 7፡37-39፤ ራእ. 22፡1-2።

ሐ. እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ትንሿ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሆን አለባት፣ እያንዳንዱ አማኝም "ትንሽ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም" መሆን አለበት፤ ከአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ጋር የሚገናኝ ነገር ሁሉ የጋራ እና የግል ልምምዳችን መሆን አለበት—21፡3፣ 22-23፤ 22፡1-2፣ 14፣ 17፣ 3፡12።

መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከፍትሃዊ እና ከሕይወታዊ ገጽታዎቿ ጋር የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን አካል መልበስ ናት—ሮሜ 5፡10፤ ራእ. 22፡14፡-

1. የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን መሠረቱ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጽድቅ እና መጠናቀቁ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሕይወት የተዋቀረ ነው—ሮሜ 1፡16-17፤ 5፡10፣ 17-18፣ 21፤ ሉቃ. 15፡22-23፣ ተዛ. ኤር. 2፡13፤ 13፡23፤ 17፡9፤ 23፡5-6፤ 31፡33።
2. መላዋ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በጽድቅ መሠረት ላይ የተገነባች የሕይወት ጉዳይ ናት—ራእ. 21፡14፣ 19-20፤ 22፡1፤ ተዛ. ዘፍ. 9፡8-17፤ መዝ. 89፡14።

ሠ. የእግዚአብሔርን ሕይወታዊ ማዳን እያንዳንዱን ክፍል ስንለማመድ፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ ማንነቶች እስከምንሆን ድረስ ደረጃ በደረጃ ከፍ እያልን እንሄዳለን—ሮሜ. 5፡10፣ 17፣ 21፤ 8፡10፣ 6፣ 11፤ ራእ. 22፡1-2፣ ተዛ. ኤር. 18፡15፤ ሚክ. 5፡2፡-

1. ለእግዚአብሔር ልጅነት የእግዚአብሔር ዝርያዎች፣ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን በእግዚአብሔር ሕይወት ውስጥ በመሳተፍ ዳግም ተወልደናል—ዮሐ. 1፡12-13፤ ራእ. 21፡7፤ 22፡14።
2. እንደ ቅድስቲቱ ከተማ ቅዱስ ለመሆን በእግዚአብሔር ባህሪ ውስጥ በመሳተፍ ተቀድሰናል—1ተሰ. 5፡23፤ ኤፌ. 5፡26።
3. እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አዲስ ለመሆን በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ በመሳተፍ ታድሰናል—2 ቆሮ. 4፡16፤ ኤፌ. 4፡23።
4. በሦስታንዱ አምላክ እንደ ወርቅ፣ ብር (ዕንቁ) እና የከበሩ ድንጋዮች ለመቀናበር በእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ በመሳተፍ ተለውጠናል—1 ቆሮ. 3፡12፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ ሮሜ 12፡2፤ ራእ. 21፡18-21።
5. የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መልክ እንዲኖረን በእግዚአብሔር መልክ ውስጥ በመሳተፍ የበኩሩን ልጅ መልክ መስለናል—ሮሜ 8፡28-29፤ ራእ. 21፡11፤ 4፡3።
6. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ክብር ሙሉ በሙሉ ጢም ብሎ ለመሞላት በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ በመሳተፍ ከብረናል—ሮሜ 8፡21፤ ፊልጵ. 3፡21፤ ራእ. 21፡11።

**III. *አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን መኖር እና መሥራት ማለት ለክርስቶስ አካል እውነታ እና ለአዲስ መነቃቃት ልዩና-ብቸኛ በሆነው በአዲስ ኪዳን አገልግሎት፣ በዘመኑ አገልግሎት ውስጠ-መሠረታዊ ንጥረ-ነገር እና ጥቅል-ድምር መሠረት የእግዚአብሔርን ሙሉ ማዳን መኖር እና መሥራት ነው—ፊልጵ. 1፡19፤ 2፡13፤ ሮሜ 5፡10፤ 2 ቆሮ. 4፡1፤ ኤፌ. 4፡11-12፣ 16፡-***

ሀ. የመንፈስ አገልግሎት በሕያው የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ መለኮታዊው እና ምሥጢራዊው "ቀለም" በልባችን ላይ በመቅረጽ፣ የክርስቶስ ሕያው መልእክቶች በማድረግ እኛን መለኮት የሚያደርግ የአዲሱ ኪዳን አገልግሎት ነው—ይህ የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛው ጫፍ ነው—2 ቆሮ. 3፡3፣ 6፣ 8፣ 18፤ 4፡1፤ ኢሳ. 42፡6፤ 49፡6፤ መዝ. 45፡1-2፡-

1. በመንፈስ አገልግሎት የሕይወት ከተማ ለመሆን እና የክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን "ክርስቶስን እየተደረግን" ነው፤ በመሆኑም፣ የእግዚአብሔር እና የሰው እንደ አንድ መንፈስ መዋሐድ የሆነን ሕይወት፣ እጅግ የላቀ እና በበረከት እና በደስታ ሞልቶ የሚፈስን ሕይወት ለመኖር መንፈስ እንደተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ሙሽራይቱን እንደተለወጠችው ሦስት ክፍል ያላት ቤተ ክርስቲያን ያገባል—ሮሜ 5፡10፤ ራእ. 2፡7፤ 22፡1-2፣ 17።
2. ለክርስቶስ አካል መገንባት የአዲሱ ኪዳን አገልጋዮች ሆኖ ለመቀናበር፣ በ 2ኛ ቆሮንቶስ ላይ ያሉትን ሁሉን-ያካተተውን መንፈስ ሁሉንም ገጽታዎች—የሚቀባው መንፈስ፣ የሚያትመው መንፈስ፣ እንደ መያዣ የተሰጠውን መንፈስ (1፡21-22፣ 5፡5)፣ የሚጽፈው መንፈስ (3፡3)፣ ሕይወትን የሚሰጠው መንፈስ (ቁ. 6)፣ የሚያገለግለው መንፈስ (ቁ. 8)፣ አርነት የሚያወጣው መንፈስ (ቁ. 17)፣ የሚለውጠው መንፈስ (ቁ. 18)፣ እና የሚያስተላለፈውን መንፈስ (13፡14)—መለማመድ አለብን።

ለ. የጽድቅ አገልግሎት ለመጽደቃችን ክርስቶስ እንደ ውጫዊ ጽድቃችን እና ክርስቶስን ለመኖር እና እውነተኛ ለሆነ የክርስቶስ መገለጥ እንደ ውስጠ-ልምምዳዊ ጽድቃችን ወደ እኛ ውስጥ በመንፈስ የመለወጥ ሥራ "የተጠለፈው" ክርስቶስ አገልግሎት ነው—ይህ የአምላክ-ሰው ኑሮ ነው—3፡9፤ መዝ. 45፡13-14፤ ሮሜ 8፡4፤ መዝ. 23፡3፡-

1. በጽድቅ አገልግሎት በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር እንደ የጽድቅ አዲስ ፍጥረት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለመሆን ክርስቶስን እንደ ውጫዊ ጽድቃችን እንቀበለዋለን እንዲሁም እንደ ውስጠ-ልምምዳዊ ጽድቃችን እርሱን እንደሰተዋለን—1 ቆሮ. 1፡30፤ ፊልጵ. 3፡9፤ 2 ጴጥ. 3፡13፤ ተዛ. ኢሳ. 33፡22።
2. ውጫዊ ጽድቅ (ለእኛ የተሰጠው ክርስቶስ) ጸጋን (የምንደሰተውን ክርስቶስ) ያመጣል፣ ጸጋ ደግሞ ውስጠ-ልምምዳዊ የሆነን ጽድቅ (ክርስቶስን መኖራችንን) ያመጣል—ሮሜ 5፡1-2፣ 17-18፤ ሉቃ. 15፡22-23።
3. የጸጋ ኃይል እኛን ከእግዚአብሔር ጋር፣ ከሌሎች ጋር እና ከራሳችን ጋር እንኳ ሳይቀር ትክክል በማድረግ በእኛ ይሠራል እንዲሁም ውስጠ-ልምምዳዊ የሆነን ጽድቅ ያፈራል፤ በሕይወት እንድንነግሥ በማድረግ ኃጢአትን ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን በማንነታችን ውስጥ ያሉትን ሰይጣንን፣ ኃጢአትን እና ሞትን ድል-ይነሣል—2 ጢሞ. 2፡1፤ ሮሜ 5፡17፣ 21።
4. ለመጽደቃችን የተቀበልነው ጽድቅ ውጫዊ የሆነ እና ጻድቅ የሆነውን አምላክ ጥያቄዎች እንድናሟላ የሚያስችል ሲሆን፣ የድል-ነሺዎቹ ቅዱሳን ጽድቅ ደግሞ ውስጠ-ልምምዳዊ እና የድል-ነሺውን ክርስቶስ ጥያቄዎች እንዲያሟሉ የሚያስችላቸው ነው—ራእ. 22፡14፤ 19፡7-8።

ሐ. የማስታረቅ አገልግሎት ለፍትሃዊ ቤዛነታቸው በኃጢአቶች ይቅርታ በኩል ዓለምን ከክርስቶስ ጋር የማስታረቅ እና ለሕይወታዊ መዳናቸው በመንፈስ፣ በቅድስተ ቅዱሳን የሚኖሩ ሰዎች እንዲሆኑ አማኞችን ከክርስቶስ ጋር የማስታረቅ

አገልግሎት ነው—ይህ በእግዚአብሔር መሠረት ሰዎችን በእረኝነት መንከባከብ ነው—2 ቆሮ. 5፡18-21፤ 1 ጴጥ. 5፡1-6፤ ዕብ. 13፡20፡-

1. የጌታ የጊዜው ምለሳ በመዝሙር 22 እንዳለው የሚዋጀው ሞቱ እና ቤተ ክርስቲያንን የሚያፈራው ትንሣኤ ውጤት እና በመዝሙር 24 ባለው መንግሥቱን ለመመሥረት እንደ ንጉሥ የመምጣቱ ፈጻሚ ምክንያት በመዝሙር 23 ወዳለው ወደ ክርስቶስ እስትንፋሳዊ እረኝነት እውነታ እኛን ለማምጣት ነው።
2. በማስታረቅ አገልግሎት ብዙዎች እንደተካተቱባት ቅድስተ ቅዱሳን፣ እግዚአብሔር እንዳለበት ስፍራ፣ ዘላለማዊዋ ጽዮን እንሆን ዘንድ እንደ የሕይወት ውሃዎች ምንጮች እግዚአብሔርን ለመደሰት በእረኝነት እንክብካቤ ወደ እግዚአብሔር ውስጥ እየገባን ነው—ራእ. 7፡14፣ 17፤ 14፡1፤ 21፡16፣ 22፤ መዝ. 20፡2፤ 24፡1፣ 3፣ 7-10፤ 48፡2፤ 50፡2፤ 87፡2፤ 125፡1፤ ሕዝ. 48፡35።
3. የማስታረቅ አገልግሎት በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መሠረት አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ የክርስቶስ አካል ትገነባ ዘንድ የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት ለመንከባከብ ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር በትብብር የሆነ የሐዋርያት አገልግሎት ነው—ዮሐ. 21፡15-17፤ ሐዋ. 20፡28-29፤ ራእ. 1፡12-13።

**IV. የጌታ ምለሳ ልዩና-ብቸኛ ወደሆነው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት መልሶ ያመጣናል፤ ይህ አገልግሎት (2 ቆሮ. 3፡18፤ 4፡1) የሚከተሉት መለያ ባህሪያት አሉት፡-**

ሀ. የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ጤናማ ትምህርት ያገለግላል እንዲሁም በእንግዳ እሳት ማለትም በሰው ተፈጥሮአዊ ትጋት፣ ተፈጥሮአዊ ፍቅር፣ ተፈጥሮአዊ ጥንካሬ እና ተፈጥሮአዊ ችሎታ ከሆኑት ከተቃዋሚዎች ልዩ እና እንግዳ ትምህርቶች ጋር መልካሙን ጦርነት ይዋጋል—1 ጢሞ. 1፡3-4፣ 18፤ ዕብ. 13፡9፤ 2 ጢሞ. 2፡1-15፤ ዘሌ.10፡1-11።

ለ. አንድ ዓይነት በሆነ ውስጠ-ነገር፣ መልክ እና መገለጥ የኢየሱስ ምስክር ይሆኑ ዘንድ አጥቢያ አብያተ ክርስትያናትን እንደ ወርቃማ መቅረዞች ያፈራል፣ እንዲሁም ሁላችንንም ወደ ሦስታንዱ አምላክ አንድነት ውስጥ ፍጹማን በማድረግ በአንዱ መንፈስ የክርስቶስን አካል ይገነባል—ራእ. 1፡10-13፣ 20፤ ዮሐ. 17፡23፤ ኤፌ. 4፡1-4፣ 11-13፤ ዘካ. 4፡6።

ሐ. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እንደ “ንጉሡ ቤተ መንግሥት” ይጠናቀቁ ዘንድ በራሱ እንደ “ንጉሣዊው መኖሪያ” እና በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ “ዝሆን ጥርሶች ቤተ መንግሥት” ድል-ነሺዎቹን የክርስቶስ ሙሽራ እንዲሆኑ ያዘጋጃቸዋል፤ እኛን የእርሱ ንግሥት ለማድረግ ለክርስቶስ ባለ ቅንነት እና ንጽሕና ለእርሱ ያለንን ፍቅር በማነሳሳት ለክርስቶስ ያጩናል—መዝ. 45፡1-15፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10፤ 2 ቆሮ. 11፡2-3።

መ. ለሕይወት መገለጥ እና መባዛት በክብር መንገድ፣ በመስቀሉ መንገድ መከራዎቹን በመካፈል ክርስቶስን እንድንከተለው ያበረታናል—ዮሐ. 12፡24-26፤ ቆላ. 1፡24፤ 2 ቆሮ. 4፡10-11፣ 16-18፤ 11፡23-33።

ሠ. በሕይወት ለመንገሥ በሕይወት እንድን ዘንድ ክርስቶስ ለእኛ ለመገለጡ፣ ክርስቶስን ለመደሰታችን እና በሕይወት ለማደጋችን ክርስቶስን እንደ ጸጋ፣ እውነት፣ ሕይወት እና መንፈስ ወደ ውስጣችን ያድላል—1፡10፣ 24፤ ፊልጵ. 1፡25፤ ሮሜ 5፡10፣ 17።

ረ. በእውነት ቃል እና በቃሉ ውስጥ ባለው ውኃ ማጠብ በኩል ይቀድሰናል፤ በተጨማሪም በእስትንፋሳዊው ክርስቶስ የሚያስደስት እና የሚመግብ መገኘት በእረኝነት ይንከባከበናል—ዮሐ. 17፡17፤ ኤፌ. 5፡26፣ 29-30፤ ራእ. 1፡12-13።

ሰ. በእውነታ አንዱ የክርስቶስ አካል እንድንሆን ሁላችንንም የክርስቶስ ወንድሞች፣ የክርስቶስ ባሪያዎች እና የክርስቶስ ብልቶች በማድረግ የሥልጣን ተዋረድን በማፈራረስ አንድ ወደ መሆን ውስጥ ያገጣጥመናል፤ ክርስቶስን በቤተ ክርስቲያን ሁሉ ነገር ለማድረግ ከፍ ያሉ ስፍራዎችን በማፈራረስ ክርስቶስን ብቻ ከፍ ከፍ ያደርጋል—ማቴ. 23፡8-12፤ 1 ቆሮ. 12፡24፤ ዘዳ. 12፡1-3፤ 2 ቆሮ. 4፡5፤ 10፡3-5፤ ቆላ. 3፡10-11።

ሸ. እግዚአብሔር-የወሰነውን መንገድ በተግባር እንድንለማመድ ሁላችንንም ወደ ማገልገል ያመጣናል፣ በምድር ሁሉ ላይ የመንግሥቱ ወንጌል ለመሰበኩ በጉ ወደሚሄድበት ሁሉ እንድንከተለው ይመራናል—ሮሜ. 12፡4-5፤ ኤፌ. 4፡11-12፤ ራእ. 14፡4፤ ማቴ. 24፡14።

ቀ. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ እንዳለ ከፍተኛ ነጥብ የክርስቶስን አካል እውነታ ለማግኘት አዲሲቷ ኢየሩሳሌምን ወደ መኖር እና አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ወደ መሥራት መነቃቃት ውስጥ ያመጣናል—2 ቆሮ. 3፡6፣ 8-9፤ 5፡18-20፤ ሮሜ 12፡4-5፤ ኤፌ. 4፡4-6፣ 16።

*© 2021 Living Stream Ministry*